IBO

IB DIPLOMA PROGRAMME
PROGRAMME DU DIPLÔME DU BI
PROGRAMA DEL DIPLOMA DEL BI

22070014

**AMHARIC A1 – HIGHER LEVEL – PAPER 2**
**AMHARIQUE A1 – NIVEAU SUPÉRIEUR – ÉPREUVE 2**
**AMHÁRICO A1 – NIVEL SUPERIOR – PRUEBA 2**

Wednesday 16 May 2007 (morning)
Mercredi 16 mai 2007 (matin)
Miércoles 16 de mayo de 2007 (mañana)

2 hours / 2 heures / 2 horas

---

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Answer one essay question only. You must base your answer on at least two of the Part 3 works you have studied. You may include in your answer a discussion of a Part 2 work of the same genre if relevant. Answers which are not based on a discussion of at least two Part 3 works will not score high marks.
- You are not permitted to bring copies of the works you have studied into the examination room.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N'ouvrez pas cette épreuve avant d'y être autorisé(e).
- Traitez un seul sujet de composition. Vous devez baser votre réponse sur au moins deux des œuvres de la 3e partie que vous avez étudiées. Le cas échéant, vous pouvez inclure dans votre réponse une discussion sur une œuvre du même genre littéraire étudiée dans la 2e partie du programme. Les réponses qui ne sont pas basées sur au moins deux des œuvres de la 3e partie n'obtiendront pas une note élevée.
- Vous n'êtes pas autorisé(e) à amener des exemplaires des œuvres que vous avez étudiées dans la salle d'examen.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Elija un tema de redacción. Su respuesta deberá basarse en al menos dos de las obras estudiadas en la Parte 3. Se podrán hacer comentarios sobre una obra de la Parte 2 del mismo género, si fuera necesario. Las respuestas que no incluyan una discusión sobre al menos dos obras de la Parte 3 no recibirán notas altas.
- No se permite traer a la sala de examen copias de las obras estudiadas.



© IBO 2007

*ከሚከተሉት በአንዱ ላይ ሀተታ ፃፍ(ፃፊ):: መልሱ በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ መመስረት አለበት:: በክፍል ሁለት ስር ከሚገኝ አንድ ተመሳሳይ የስነጽሁፍ ዘርፍ ማጣቀሻ ማስገባት ይፈቀዳል:: በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ ያልተመሰረተ መልስ ከፍተኛ ነጥብ አያስገኝም::*

**ድራማ**

1. ተከታዩን

(ሀ) ኮመዲም ሆነ ትራጀዲ የሚገነቡት በግጭት ውስጥ በሚኖረው ዋና ገፀባህሪ ዙርያ ነው:: ያጠናሃቸውን ስራዎች በመጥቀስ ይህንን ሃሳብ አስረዳ:: መልስህ ደራስያኑ ግጭቶችን ያቀረቡበትን ሁኔታ የሚያወዳድር ይሁን::

ወይም ቀጣዩን ምረጥ::

(ለ) ብዙዎቻችን ድራማ ስንመለከት የምናየውን እናምናለን:: በመሆኑም በመድረክ የሚቀርበው ሁሉ በተዋንያን የሚቀርብ ፈጠራ እንጂ በትክክል የተከሰተ አለመሆኑን ለመርሳት እንሞክራለን:: የዚህን ሃሳብ ትክክለኛነት ያጠናሃቸውን ሁለት ድራማዎች በመመርኮዝ ግለጽ:: ደራስያኑ አንባብያንንም ሆነ ትያትር ተመልካቹን ተውኔቱ ፈጠራ መሆኑን እንዲረሱ የሚያደርጉበትን ዘዴዎች አብራራ::

**ረጅም ልቦለድ**

2. ተከታዩን

(ሀ) በረጅም ልቦለድ የልብ መሰቀል (ሰስፔንስ) የሚጨምረው በአንባቢው የሚወደድና የሚታዘንለት ገፀባህሪ ምን ይገጥመው ይሆን በሚል የማወቅ ጉጉት ሲፈጠር ነው:: ያነበብካቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በማነፃፀር ይህንን ሃሳብ ግለጽ::

ወይም ቀጣዩን ምረጥ::

(ለ) ማንኛውም ጥሩ የልቦለድ ፀሃፊ የልቦለዱን ዋና አላማ ወደፊት የሚያራምዱ ጉዳዮች ብቻ መርጦ በማስገባት ይታወቃል:: ያጠናሀቸው ሁለት ደራስያን በዚህ ረገድ ምን ያህል ተዋጥቶላቸዋል?

**ስነግጥም**

3. ተከታዩን

(ሀ) ገጣሚው አንባብያን ቀድሞ የሚያውቁትን ጉዳይ ይበልጥ እንዲገነዘቡ ያደርጋል:: በዚህም አንባብያኑ እራሳቸውን እንዲያውቁ ይረዳቸዋል:: ባነበብካቸው ሶስት ግጥሞች ውስጥ ይህንን ግንዛቤ የሚፈጥሩትን ሁኔታዎች አብራራ::

ወይም ቀጣዩን ምረጥ::

(ለ) ማንኛውም ገጣሚ የሚሰማውን ፣የሚያየውንና በምናቡ የሚስለውን ገጠመኝ መርጦና አቀናጅቶ ያቀርባል:: ይህንን ሀሳብ ያነበብካቸውን ሶስት ግጥሞች በመጥቀስ አስረዳ::

**ዝርው (ከረጅምና አጭር ልቦለድ ሌላ)**

4. ተከታዩን

(ሀ) ማንኛውም ዝርው ጽሁፍ(ለምሳሌም ወግ) የተለየ ቅርጽ ያለው የተወሰነ ዐላማ ለማሳካት የሚቀርብ በመሆኑ ነው:: ይህንን አረፍተ ነገር ያጠናሃቸውን ሁለት ስራዎች በመመርኮዝ ግለጽ::

ወይም ቀጣዩን ምረጥ::

(ለ) የዝርው ጽሁፎች (ለምሳሌም ወጎች) ፀሃፊ አንባቢውን የሚያሳምነው በሚያቀርበው መረጃ ብዛትና ጥራት ነው:: ይህንን አረፍተ ነገር በሁለት ስራዎች ምሳሌነት ግለጽ::

**አጭር ልቦለድ**

5. ተከታዩን

(ሀ) በአጭር ልቦለድ አንባቢውን እንዲደነቅ የሚያደርገው ከሚጠበቀው ውጪ በታሪኩ ውስጥ እንግዳ የሆነ ክስተት ሲፈጠር ነው:: የዚህን ሃሳብ ትክክለኛ መሆንና አለመሆን ያጠናሃቸውን ሶስት ስራዎች በምሳሌነት በማወዳደር አሳይ::

ወይም ቀጣዩን ምረጥ::

(ለ) የአጭር ልቦለድ ገፀባህሪያት ባህርያቸው ያለምክንያት መለዋወጥ አይገባውም:: ይህንን ሃሳብ ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በማወዳደር አስረዳ::

**ሁለገብ (አጠቃላይ)**

**6.** ከሚከተሉት አንዱን መርጠህ መልስ(ሽ)::

(ሀ) ደራስያን የስራቸውን ጭብጥ መግለጽ ብቻ ሳይሆን የሚያነሱትን ጉዳይ ሕይወት ሰጥተው ሊያቀርቡት ይገባል:: ያጠናሃቸውን ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በመጥቀስ ሀሳብህን ግለጽ::

*ወይም*

(ለ) የስነጽሁፍ ስራ ስናነብ የደራሲው ምናባዊ እይታ ለህይወት ካለን አመለካከት የተለየ ቢሆንም እንኳዋ ስራውን ያለተጽእኖ ለመመልከት መሞከር ይኖርብናል:: ሀሳቡን በሁለት ምሳሌ አብራራ::

*ወይም*

(ሐ) ደራስያን ቢፈልጉ በገፀባህርያቶቻቸው እእምሮ ውስጥ የሚከናወነውን ሁሉ ለአንባብያን የማሳየት ችሎታ አላቸው:: ያጠናሃቸውን ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በመጥቀስ ሀሳብህን ግለጽ::

*ወይም*

(መ) የስነጽሁፍ ጭብጥ የህይወትን ገጽታ አጠቃሎ የሚያቀርብ ነው:: ያነበብካቸውን ሁለት ስራዎች በመጥቀስ ይህንን ሃሳብ አስረዳ::